ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ

**Coalition for Unity and Democracy Party (Kinijit)**

http://www.kinijitethiopia.org

e-mail kil@kinijitinternational.org Voice Mail/Fax 1-206-203-3974

ጋዜጣዊ መግለጫ **ኪል 017-07**

ሰኔ 4 1999 ዓ.ም

# ወያኔ በእብሪተኛነት የሚፈጽምው ግፍ በተባበረ ትግል መገታት አለበት

ዛሬ ሰኔ 4 1999 አ.ም መለስ ዜናዊና ወያኔ ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚፈጽሙት በእብሪት የተሞላ ግፍ ገደብ ያጣበት ደረጃ መድረሱ የታየበት እለት ነው:: በዛሬው እለት ያስቻለው በመለስ ዜናዊ ሎሌዎች የተሞላው ፍርድ ቤት የኢትዮጵያ ህዝብ በሰላም በአንድነት በእኩልነት የመኖር ተስፋውን፣ ከድህነት ከበሽታ ከሃገራዊ ውርደት መላቀቂያ ራእዩን ሰንቀው በተነሱት ህዝብም አመኔታውን በግንቦቱ ምርጫ በሰጣቸው ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጆች ላይ በዛሬው እለት ከእድሜ ልክ እስከ ሞት የሚያስፈርድ የጥፋተኛነት ብይን ሰጥቷል::

በሃሰት የተወነጀሉት የቅንጅት መሪዎች የቀረበባቸውን የሃሰት ማስረጃ በማጤን ላይ እንደከረሙ፣ ማስረጃዎቹ ተሟልተው እንዳይደርሷቸው የፍትህና የወህኒ ቤት አስተዳደሩ እየፈጸመ ያለውን በደል በሚመለከት ዳኞቹ አቤቱታቸውን እንዲያደምጡ በሚማጸኑበት ወቅት የችሎቱ ዳኞች ይህን ተማጽኖ በማቋረጥ ለአስር ደቂቃ ግዜ ስጡን በማለት ከችሎት በመውጣትና ከሁለት ሰኣት በኋላ በመመለስ የፍትህ ሂደቱ ባልተጠናቀቀበት ጉዳይ ላይ ብይናቸውን አሳረፉ:: ይህ በዛሬው ዕለት ፈጽሞ ያልተጠበቀ ብይን የተላለፈው ዳኞቹ ከችሎት ተነስተው ለሁለት ሰአታት ያህል ከወያኔ መንግሰት ባለስልጣናት ጋር በመመካከርና ከወያኔ ባለስልጣናት በተሰጣቸው መመሪያ መሰረት እንደሆነ ታውቋል::

ይህ ዛሬ በቅንጅት መሪዎች ላይ የተወሰነ የእብሪት ውሳኔ በኢትየጵያ ህዝብ የሃገር ፍቅር፣ የፍትህ የነጻነት የአንድነትና የብልጽግና ፍላጎት ላይ የተፈጸመ ጥቃት ነው:: ኢትዮጵያንና ህዝቧን ለማዋረድ፣ በሃገርና በወገን ኪሳራ የግል ኪሳቸውን በዘረፋ ለመሙላት ኢሰብአዊ ወንጀል እየፈጸሙ ለመኖር ቆርጠው በተነሱ ጸረ- ኢትዮጵያ ሃይሎች የተከወነ ነው:: የኢትዮጵያን ሕዝብ የነፃነት ትግል ገድሎ ዘላለማዊ ባርነትን በጸጋ ተቀብሎ እንዲኖር ለማድረግ ነው:: ይህ በሃገራችን ታሪክ በእብሪተኛ ነቱ ተወዳዳሪ የማይገኝለት የወያኔ ገዥዎች ውሳኔ በሃገር ውስጥም ከሃገር ውጭም የሚገኘውን ኢትዮጵያዊ የሚያስቆጣ ለበለጠ ትግል የሚያነሳሳ ነው::

ወያኔ ሰላም ሲሉት ጠብን፣ አንድነት ሲሉት መከፋፋልን፣ ስልጡን ፖለቲካ ሲሉት የዘመነ መሳፍንት ጎጠኛ በቀለኛነትን፣ ቀና ህልም ሲሉት ሆዳምነትን በማስቀደም፤ ትእግስትን ፍራቻ፣ መቻቻልን ቂልነት አድርጎ እየተረጎመ የህዝብን እልህ እንደሴጣን በመፈታተን ላይ ይገኛል:: ይህ ሞልቶ የፈሰሰው የወያኔ ግፍ ያንገፈገፈው ህዝብ በቃኝ ብሏል:: ዛሬ ከመትረየስና ከታንክ ጀርባ ተደብቀው በእብሪት ህዘብን ምን ታደርገኛለህ በማለት ደሙንና እምባውን በዋንጫቸው እየሞሉ የሚያጋጩት ገዥዎች መጨረሻቸው እንደ ትናንትናዎቹ የሀገራችን አምባገነኖች እንደማያምር እናውቃለን::

የኢትዮጵያ ህዝብ ሃገሩን፣ ክብሩን፣ ነጻነቱንና ሃብቱን እንደብል እየበሉ ለመጥፋት ቆርጠው የተነሱትን የጨለማ ዘመን ሰዎች ተሸክሞ የሚሄድበት ጫንቃ የለውም:: የዛሬው የግፍ ፍርድ፣ ሀዝብ ይህንን ሸክሙን ለማቃለል በሚያደርገው ትግል ውስጥ ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ግንባር ቀደም ሚና እንዳይጫወት የሚያሰናክለው አይሆንም:: ይበልጡንም የቅንጅት አባልና ደጋፊ

የሆነውን በሙሉ በግፍ የታሰሩ መሪዎቻችንን ራእይ፣ ጥበብና አስተምህሮት ሰንቀን፣ ወቅቱ የሚጠይቀውን ማስተካከያ በብልሃት አክለን መጪው መራር የትግል ዘመን የሚያመጣውን ፈተና ለማለፍ መደረግ የሚገበውን ሁሉ ለማድረግ በቁርጠኛነት እንድንነሳ ያደርገናል እንጂ።

የኢትዮጵያ ህዝብ በዘር በሃይማኖት ሳይከፋፋል፣ ስልጣንና ከስልጣን  የሚገኝን ተጠቃሚነት ላለማጣት ሃገራችንን ወደ ከፍተኛ የቀውስ አዘቅት እየከተተ የሚገኘውን ዘረኛና አምባገነን የወያኔ አገዛዝ፣ «በቃኝ፤ ከጫንቃየ ላይ ውረድልኝ» ብሎታል። በግንቦት 97 ምርጫ በማያሻማ ቋንቋ በምርጫ ካርዱ ያስተላለፈው መልእክት ይህንኑ ነው። በእብሪት የተደፈነው የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ጆሮ ግን አልሰማም ብሏል። በበቀል የታጀለው ልብና በጆብደኝነት የደነደነው አዕምሮ የሕዝብ ጩሐትንና የአገርን ውድቀት ሊያሳያቸው አልቻለም።  ይህንን ድምጹን ወያኔ እንዲሰማው ለማድረግ መወሰድ ያለባቸው ተጨማሪ የተግባር እርምጃዎች ለመውሰድ ዝግጁ መሆን ይኖርበታል። ይህንን ህገ-መንግስታዊ የህዝብ ውሳኔ በጉልበት በመጣስ፣ ህገ ወጥ በሆነ መንገድ፣ እንዳሻው እየገደለ፣ እያሰረ፣ እያሳደደና እየዘረፈ በፍትህና በህግ ስም ያለምንምም ይሉኝታ ለሚያቅራራ አጉራ ዘለል መድሃኒቱን መሻት የኢትዮጵያ ህዝብ እንደማይጠፋው እናውቃለን። ይህ ገደብ ያጣና መረን የለቀቀ የወያኔ ዕብሪተኞች ዕርምጃ ዛሬ ለነጻነቱ ቀናዒና ለመብቱ ሟች በሆነው ህዝባችን ሊገታ ይገበዋል።

በሃገር ውስጥና በሃገር ውጭ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን በሙሉ የቅንጅት መሪዎች ተሸክመው የሚሰቃዩለት ራእይ የሃገርና የወገን ራእይ እንጂ የአንድ ፖለቲካ ድርጅት ራእይ አለመሆኑን ተገነዝበን፣ የዛሬውን የግፍ ብይን በጋራ ለመኮነን፣ እነዚህ ብርቅዬ የህዝብ ልጆች መስዋእትነት እየከፈሉለት ያለው የነጻነት፣ ዴሞክራሲና የፍትህ ጥያቄ በወያኔ ሊታሰርና ሊገደል የማይችል መሆኑን ለዘረኛውና አምባገነኑ ወያኔ በጋራ ድርጊት ማረጋገጥ ይጠበቅብናል።

**ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ**